# አገር በቀል ፍሬ!!

በአገረ ኢትዮያ፣ በአበሻ ምድር
ከጦቢያ እምብርት፣ከውቢቱ ሽገር፤
ከቆላ አሰከ ደጋ ከመሃል እስከዳር፤
ከሜዳ ከጋራው፣ ከተረተሩ ሥር፤
ከወይና ደጋማው፣ከነፋሻው መንደር፤
ከዋርካው፤ ከወይራው፣ከዕንቆቆው ሰፈር፤
ከጥድ ከዝግባው ጋር፣ተመሳስላ በህብር
አገር በቀል ተክል፣ምርጥ የዕጸዋት ዘር፤
የብርቱካን ፍሬ፣ ሽታዋ ሰው- አፈር፤
ስሟ የገነነ፣ጥቅሟ የታወቀ፣ባለ ብዙ ምስጢር፤
ዛፍ ቆራጩ ነቅሏት፣ኋላ እንዳንቸገር፤
**የህዝብ ተክል ናት፣ጠንቀቅ በል ባላገር::**

ከዕጸዋት ዘር ሁሉ፤ ጣፋጭ ከፍሬዎች፤
ከአታክልቶች ሁሉ፣ ፍሬ ጭማቂዎች፤
የቪታሚን ቅመም፣በውስጥዋ የያዘች፤
ለብርድ ለጉንፋን መድሃኒት የሆነች፤
ለሙሉ ጤንነት፣ዋስትና የሆነች፤
ተስማሚ ለጤና፣ ተወዳጅ በሰዎች፤
የብርቱካን ፍሬ፣ የሕዝብ ሀብት ነች፤
**በህብረት ኮትኩቷት፣አደራ ወገኖች::**

መንፈስ አነቃቂ፣ ፍኖተ ዘፍጥረት
ፈውስ ለበሽታ፣የአበሻ መድሃኒት፤
መዓዛ ሽታዋ፣የሚዘራው ሕይወት፤
በጫካው ውስጥ ያለች፣በሩቅ የምታዩአት፤
የታደለች ውበት፣ ብርቱካን-ሎሚናት፣
ሐረግ መዛገቿ፣ ዓይን እንደጣሉባት፤
በ«ምርጥ ዘር» ጣጣ፤ ነቅለው እንዳይጥሏት፤
ወገኔ ተረዳድተህ፣ **ከዕጅ-ሰብ** ጠብቃት፤
**ቀጣፊው_ብዙ ነው፣ዓይኑን የጣለባት::**

እኒህ መንገደኞች፣ አጥር የሚገፉ፤
ሰው በሰው ሊጥሉ፤ሆነው የሰው ክፉ፤
መኖርን ሙያ አርገው፣ ሰው እየዘረፉ፤
ምክር አልሰማ ብለው፣ እጅ ቢያሳርፉ፤
ያን የብርቱካን ተክል፣ ያን ፍሬ ቢቀጥፉ፤
ሞልቶ ተርፎ እንዳይፈስ፣ እጅግ በዝቶ ግፉ፤
ቂም በቀል ጥላቻ፤ ሆኖ እንዳይቀር ትርፉ፤
**ብላችሁ ንገሩ፤«ዝም ብላችሁ እለፉ::»**

አገር በቀል ፍሬ፤አገር በቀል አትክልት፤
ቅጠሏ አረንጓዴ፣የሀብት ምልክት፤
ፍሬዋ ወርቃማ ፣የፍቅር ግብአት፤
ቅርንጫፏ ህብር፣ትስስር የአንድነት፤
ሰንደቅ ነው ግንዷ፣አርማው የቆመበት፤
ሥሯ የጠለቀ፣መሠረተ ሕይወት፤
መዓዛ ሽታዋ፣ ያለው ፍቱንነት፤
ለታመመ ሁሉ፤ የምትሆን አብነት፤
**የአዝርዕቶች ቁንጮ፤የፍሬዎች ንግስት፤**
**የሰው ፍሬ ብቅል፣ብርቱካንን እዩአት::**

በጣይቱ ጓሮ፣ በነወንዲራድ፤
ተተክላ በመንፈስ፣ በሸዋ-ረገድ፤
በዚያች የሴት ጀግና፣ታጣቂ ባሩድ፤
አጭር ሱሪ ለባሽ፣ሥራ አገር ወዳድ፤
ነጭ በሬ ጠምዳ፣ ስታንጎራድድ፤
ገድሏ የተጻፈ፣ባገር ታሪክ አምድ፤
ይህችንስ ብርቱካን፣ አደራ ጠብቁ፤
መድሃኒት አጥታችሁ፣ በኋላ እንዳታልቁ::

«የበቀለች ተክል፤ ከጥቁር መረሬ፤
ወፍ ዘራሽ ያልሆነች፣አገር በቀል ፍሬ፤
የተኮተኮተች፣ በወንዜ ገበሬ
የክፉ ቀን መውጫ፣ ቀሪ ሀብቴ ክብሬ፤
ተስፋዬ በሷ ነው፣ መኖሬ ባገሬ፤
አልሰጥም በጭራሽ፣ በህይወቴ ኖሬ፤»
ብለህ በል ተነሳ፣ ከተሜ ገጠሬ፤
ብርቱካን! ብርቱካን!፣ እንዲሸት አገሬ::

ከኃይለማርያም ለገሰ
ጥር 1998